# አግአዚ ሰራዊት እና የአግአዚ ልጅ

ሲሣይ አጌና

መጋቢት20/2003 ምሽት ኮምፒውተሬን ስበረብር የታጋይ ዘርዑ ገሰሰ//አግአዚ ልጅ ትብለፅ ብቅ አለች፤ፎቶግራፉዋ ማለቴ ነው፤አግአዚን ሳስታውስ ደግሞ የሰኔ 1997ቱ እና የጥቅምት/ሕዳር 1998ቱ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ መጣብኝ፤...የአግአዚ ክፍለጦር አባል የነበረውና ቃሊቲ ከእኛ ጋር አንድ ቤት ታስሮ የነበረው ሞላም ከፊቴ ድቅን አለ፤የጉዋደኛው ኪሮስ መገደልና የርሱ የእስር ሁኔታ እንዲሁም የአግአዚ ሰራዊት የተደራጀ ግድያም ትዝ አለኝ፡፡ትብለፅ በግድያው ሰሞን ለ ***ኢትኦጵ*** ጋዜጣ የሰጠችውን ቃለምልልስ ከ 5 ዓመት በኂላ ደግሜ ሳነብ ለዚህ አረመኔያዊ ድርጊት የሕወሓት ደጋፊዎች ጥብቅና ይበልጥ አናደደኝ፤የሕወሓት ደጋፊዎች ሥርዓቱን በፖሊሲው ቢደግፉት አመለካከት ነውና ዕዳው የሃሳብ ትግል ነው፣ለዚህ አረመኔያዊ ድርጊት አረመኔዎቹ ሰበብ ፍለጋ መዳከራቸው የሚጠበቅ ቢሆንም፣ደጋፊዎቹ ቢያንስ በዝምታ ፣ቢቻል በማውገዝ ሰው መሆናቸውን ማስመስከር ይጠበቅባቸው ነበር፤እየሆነ ያለው ግን ገዳይን ማውገዝ ሳይሆን ሟችን መውቀስ መለያቸው ሆኗል፤.አንድ አብነት ላንሳ፡፡

ሚሊዮኖች የሚያደምጡት የቮይስ ኦፍ አሜሪካ አድማጮች ***«በለው ነኝ ከካናዳ »***እያሉ ዘወትር ለሕወሓት ጥብቅና የሚቆሙትን ሰው ያስታውሱዋቸዋል እና ለተነሳሁበት ጉዳይ ጥሩ ምሳሌ ናቸው፤የግብፅ ወታደሮች ጨዋነትና ገለልተኛነት እየተነሳ ከኢትዮጵያው የ1997 ጭፍጨፋ ጋር እየተወዳደረ መቅረቡ ያናደዳቸው እኚህ ሰው የሰጡት አስተያየት የአግአዚን ጦር ጀግንነት የሚያወሳና ቅንጀትን የሚከስ፣አደባባይ የወጣውን ሕዝብ የሚወቅስ ነበር፤የግብጽ ሕዝብ ሰላማዊ ስለመሆኑም ነግረውናል፡፡

ቅንጀት ሰልፍ ጠርቷል፣አልጠራም የሚለውን ለግዜው እሱን እንተወው፤የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከግብጽ ሕዝብ በላይ ሰላማዊ መሆኑን የሚያዚያ 30/1997ን ሰልፍ ላየ ወይንም ለሰማ ሌላ ማረጋገጫ አያስፈልግም፤የሰኔ አንዱ ግድያ እንዴት እንደተቀነባበረ ታሪክና ምርመራ ያወጣዋል፤ከጥቅምቱ 22 ግድያ 1 ቀን በፊት የማዕከላዊ ምርመራ እስር ቤትን ባዶ በማድረግ የተደረገው ዝግጅትና ግጭቱ የተፈጠረበት ሁኔታ፣ሌላው ቀርቶ ፖሊሶቹ በማን እንደተገደሉ ኢትዮጵያ በሕግ መመራት ስትጀምር ይደረስበታል፤ሰልፍ የወጣው ዜጋ ፀረ ትግሬ እንደሆነ ተደርጎ እየተለፈፈ ብዙ ቀፋፊና ሃላፊነት የጎደላቸው ንግግሮች ከሕወሐት መሪዎች አንደበትም አድምጠናል፤ እነርሱና ደጋፊዎቻቸው ዘመን መሻገር አቅቷቸው ጎሳ ኩሬ ውስጥ ሲንደፋደፉ አዲሱ ትውልድ ሕብረብሔራዊነትንም ተሻግሮ ዓለማቀፋዊነትን እየዘመረ፣የዕውቀትን ባህር እየበረበረ በሉሲ ዘመን ሰዎች እያፌረ ይገኛል፤

የሚያዚያ 30ውን ሰልፍ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የእለቱ ዕለት የተመለከቱ እንደሚያስታውሱት ጓደኞቹ ተሸክመውት መፈክር ሲያሰማ እና ሼህ ሞሃመድ አላሙዲንን ሲያወግዝ የሚታየው **ክብሮም ዮሃንስ** አዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ፣እናቱም አባቱም የትግራይ ተወላጆች ናቸው፤እንደሌላው ሁሉ በመንግስት ግልበጣ እንዳያስሩት እድሜው ስላልደረሰ ከወራት በኂላ አደገኛ ቦዘኔ ብለው ሸዋ ሮቢት እስር ቤት በመስደድና ከትምህርቱ በማፈናቀል በቀለኛነታቸውን አሳይተዋል፤..ክብሮምን በዚያኑ ሰሞን ፈልገን አግኝተን በጋዜጣችን ላይ ቃለ ምልልስ ባደረግንለት ወቀት ***«አንዳንድ እናቶች ዘራችንን ሰደብክ ብለው ቅር ብሎአቸዋል፤ ሌላው ግን አድንቆኛል»*** *ነበር ያለው፡፡.እናቶቹስ ..ምን ያድርጉ በቀበሌ ካድሬ እየተጠቀጠቁ፤...ለመሆኑ አላሙዲን የሚባል ዘር በኢትዮጵያ አለ እንዴ?በአለምስ ላይ ቢሆን፤....*

*በዚሁ በምርጫ 97 ሰሞን አባት በኦነግነት ተጠርጥረው ቃሊቲ፣ልጅ በቅንጅትነት ታፍሶ ዝዋይ የተወሰደበትን ሁኔታ እዚህ ላይ ማንሳቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ቢጀመር የዘር ፍጅት ይፈጠራል በሚል ለሚያስፈራሩ እና በቅንነት ለሚሰጉ የራሱ መልዕክት አለው ብዬ አምናለሁ፤አውሮፕላን አስነስተው ሊጨፈጭፉን ይችላሉ በሚል ለሚሰጉ ወገኖቼ በተወሰነ ደረጃ ሥጋታቸውን የምጋራ ቢሆንም፣እንኳዋን በጄት ደብድበው ሽጉጥም ተኩሰው መሸሻ ስለማይኖራቸው ማሰብ እንደሚጀምሩ ይታመናል፡፡*

*አውሮፕላን አስነስቶ እንዲደበድብ ሲጠየቅ ምላሽ የሰጠ አብራሪ በትንሹ በራሱ ላይ የእድሜ ልክ እስራት መፍረድ በመሆኑ፣በራሱ ላይ ሞትን የሚጋብዝ ጤነኛ አብራሪ ይኖራል ተብሎ አይታመንም፤ዘረኝነት ከጤና የሚያወጣ በመሆኑ በጥላቻ ምላሽ የሚሰጥ አብራሪ አይኖርም ብሎ መደምደም ያስቸግራል፤...ለእንደዚህ ዓይነቱ ማሳሰብ የሚያስፈልገው አዲስ አበባ የ 170 ሺ የትግራይ ተወላጆች መኖሪያ ጭምር መሆኑዋን ነው፡ነው፡፡«ልማታዊው መንግስታችን»መቼም ብሄር ብሄረሰብ እየለየ የሚመታ ቦንብ እንዳልፈበረከ ይታመናል፡፡..እነ አቶ መለስ ወንበራቸው ጤና ይሁን እንጂ ማንም ቢያልቅ ግድ የሚላቸው ዕለቂቱ የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንጂ ሰብዓዊነት እንዳልሆነ 20 ዓመት ሙሉ በደንብ ተናበናል፡፡...ይልቅ እንደ አቶ በለው ያሉት የሚሰጡት ጭፍን ድጋፍ፣የሕወሓት መሪዎች በተለይ ከምርጫ 97 በኂላ የሚከተሉት ፍጹም ሚዛኑን የሳተ ዘረኝነትና አድሎዊነት የሕዝቡን ትዕግስት ከመጠን በላይ እየተፈታተነ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማስገንዘቡ አይከፋም፡፡*

*መነሻዬ በአረመኔነቱ ሀገር አቀፍ ዕውቅናን ስለተጎናጸፈው አግአዚ ክፍለጦር የአግአዚ ልጅ በወቅቱ በሃምሌ 1997 የሰጠችንን ቃለምልልስ በማቅረብ ጭፍን ደጋፊዎች ህሊናቸውን እንዲመረምሩ ለማገዝ ቢሆንም፣ብዙ ዝርዝዝር ውስጥ ገባሁ፤(የነሞላን ጉዳይ በሌላ ግዜ አመለስበታለሁ) እዚህ ላይ ይብቃኝና የ* ***ኢትኦጵ ጋዜጣ*** *ባልደረባ የነበረውና አሁን በሕንድ ሀገር የሚገኘው* ***አርኣያ ተስፋማርያም*** *ትብለጽ ዘሩን (የአጋዚን ልጅ) በማነጋገር አጠናቅሮት የነበረውን ዘገባ እንድትመለከቱት እጋብዛለሁ፡፡*

**lualawi2000@yahoo.com**

## «በአባቴ ስም የተሰየመው ጦር የፈፀመውን ድርጊት ስሰማ በጣም ይቀፋኛል»
## የአግአዚ ልጅ ትብለፅ ዘርዑ




...ወላጆቹ ያወጡለት ስም ዘርኡ ነው:: ለእናቱ ብቸኛ ወንድ ልጅ የሆነውና አንድ ልጅ ብቻም የወለደው ወይም ተክቶ ያለፈው ዘርኡ ገሰሰ ከመጀመሪያቹ የሕወሓት ታጋዮች አንዱ ሲሆን፣ በአብዛኛው የትግል ጓደቹ የሚታወቀው አግአዚ በሚለው የበረሃ ስሙ ነው:: በ1967 ዓ.ም የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ የጀመረው አግአዚ በዚሁ ተግባር ላይ እያለ በመጋቢት 1968 ዓ.ም በአክሱም ውቅሮ ማራይ በተባለ ስፍራ ከደርግ ሕዝባዊ ሰራዊት ጋር በተደረገ ጦርነት ሕይወቱ አልፏል:: እንደአጋጣሚ ሆኖ አግአዚ የሞተው የትውልድ ስፍራው በሆነችው ውቅሮ ማራይ ሲሆን፣ በዚህችው መንደር አንዲት ሴት ልጅም አፍርቶ ነበር::

...የአግአዚ ልጅ ትብለፅ ትባላለች:: በ1966 ዓ.ም የተወለደችው ትብለፅ፣ ከወላጅ አባቷ ጋር ገና ጨቅላ ሕፃን እያለች ነበር የተነጣጠሉት:: በአንድ ዓመቷ ተለይቷት ወደ ትግል ዓለም የገባው አግ አዚ፣ ልጁ ትብለፅ የሁለት ዓመት ሕፃን እያለች ነበር ሕይወቱ ያለፈው::

...እድሜዋ ከፍ እያለ ሲሄድ እንደማንኛውም ልጅ አባቷን የማየትና የማግኘት ጉጉትና ናፍቆት ያደረባት ትብለፅ፣እናቷን መጠየቅና መወትወት ትጀምራለች::ሆኖም እናቷ ጥያቄው በተነሳ ቁጥር የምትሰጠው ምላሽ የተድበሰበሰ ከመሆኑም ባሻገር ሁሉንም ነገር ትብለፅ ስታድግ እንደምትነግራት ትገልፅላት ነበር::

...የአግአዚ ልጅ ትብለፅ ከወላጅ እናቷና ከ6 የመንደሯ ልጆች ጋር በመሆን ከትግራይ ወደ ኤርትራ ምድር ይሰደዳሉ:: በአስመራ ኑሮን መግፋት የጀመረችው ትብለፅ ከእናቷ ጋር ሆና እስከ 1979 ዓ.ም ትምሕርቷን ስትከታተል ትቆያለች:: በዛ ወቅት እናቷ ስለአግአዚ ሞት ከሌሎች ሰዎች ጋር ስት ጫወትና አሟሟቱን ስትናገር ትብለፅ በአጋጣሚ (ተደብቃ) ታደምጣለች::....ከዚያም ከአራት ሴት ጓደ ኞቿ ጋር በመሆን ወደ ትግል በረሃ ያመራሉ:: እንደትብለፅ ጥቆማ በወቅቱ ለመታገል የወሰነችው አባቷ ለሕዝቦች መብትና እኩልነት ሲል የከፈለውን መስዋዕትነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባቷና የአግአዚን አርአያ ለመከተል እንደሆነ ትናገራለች::

...ከዚያም በምሽት ጉዞ ላይ እንዳሉ  መንደፈራ ፍተሻ ኬላ ላይ በወታደሮች ይያዛሉ:: ለጠላት መረጃ ልታቀብሉ ነው ተብለው ታሰሩ:: በተለይ ትብለፅ ከፍተኛ ድብደባ የተፈፀመባት ሲሆን፣ አሁን ድረስ በ አካሏ ያለው ጠባሳ ይሕንኑ ያመለክታል:: ለአንድ ዓመት የታሰሩት

*ትብለጽና ጓደኞቿ ከመሃል አንዷ ስትረሸን፣ እሷ ግን በአንድ ወታደር እገዛ ከእስር ቤት በመውጣት ከሞት ለመትረፍ ቻለች:: ሕይወቷን በማዳን ከተባበራት ወታደር ጋር ወላጅ እናቷ እንዳጋቢት ትብለፅ ትናገ ራለች::*

*...በ1983 ዓ.ም ትብለፅና ባለቤቷ እንዲሁም እናቷ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ:: ሰራዊቱ በመ በተኑ ስራ የፈታው የትብለፅ ባለቤት ኑሮን ለማሸነፍ በዘበኛነት ይቀጠራል::...ሁለf ልጆች ካፈራችለት ባለቤቷ ጋር ሞት የተባለው የሰው ልጅ ጠላት ያለያያቸወዋል:: ምንም መተዳደሪ ያ ያልነበራት የአግአዚ ልጅ ትብለፅ ከፍተኛ ችግር የሆነባት መጠለያ (ቤf) ማጣቷ ነበር:: ከሕፃናት ልጆቿና ከእናቷ ጋር ለከፋ አጣብቂኝ የተዳረችው ትብለፅ የመንግስf አነስተኛ ክፍል ቤት ለማግኘት በየአቅጣጫው ጥያቄ ማቅረብ ትቀጥላለች:: እንደአጋጣሚ በ1985 ዓ.ም ከሃየሎም አርአያ ጋር የመገናኘት እድል ይፈጠራል:: ከዚያም የመንግስት እንድታገኝ ሃየሎም ተባብረዋትና ከእናቷና ልጆቿ ጋር ትገባለች::*

*...ትብለፅ እናትዋ በሚያደርጉf የግል መፍጨ ርጨር ኑሮን ሲገፉ ከቆዩ በኋላ በ1991 ዓ.ም እናቷ ለአልጋ ቁራኛ ይዳረጋሉ:: ስለሁኔታው ትብለፅ እንዲሕ ትላለች:- «እናቴ እየታመመች፣ ወጪውም እየከበደ በመምጣቱ የቤት ኪራይ እንኳ መክፈል የማንችልበት ደረጃ ተደረሰ:: ከዚያም እናቴ ሕመም ስለፀናባት ሳትድን ቀረች:: እናቴ በሞተች በዓመቱ ከቤቱ እንድንወጣ ተ ደረገ:: ምንም መውደቂያ አልነ በረኝም::»...*

*...ለአሳዛ የመከራ ሕይወት ከነልጆቿ የተዳረገችውና የተደራረበ ችግር ብሎም ሃዘን ውስጥ የገባ ችው fብለፅ፣ በጣም እንደተጐዳችና እንደተንገላታች ያለችበት ሁኔታ ይመሰክራል:: ኑሮ ክፉኛ አጐሳቁሏታል:: በዛው መጠን የውስጥ (ሕሊና) ጉዳት እንደደረሰባት ያስታውቃል፤...አንገቷን አቀርቅራ ከአንደበቷ በምታወጣቸው ቁጥብ ቃላቶች የበለጠ አንጀትን ትብላለች::...ጐዳና የተወረወረችው ትብለፅ ከገጠማት መከራና ችግር በተጨማሪ ክፉኛ የልብ ሕመም ያሰቃያታል:: እንዲሕም ሆና በሰው ቤት በተመላላሽነf ለመስራት ትፍጨረጨራለች:: የትብለፅ ችግር በጥቂቱ ሲቆነጠር ከላይ ያለውን ሲመስል፣ በአንፃሩ ያልደረሰችበf የሕወሓf/ኢሕአ ዴግ ባለስልጣን ቢሮና ሌላው ቀርቶ የመንግስት ቤት እንዲሰጣትና የፅዳት ስራ ለማግኘት ስትል ደጅ ያልጠናችው ሹም አልነበረም:- እንደ ትብለፅ ገለፃ:: ሆኖም ከድካም በቀር ምንም ያገኘችው ውጤት አልነበረም::*

*ከዓመታት በፊት ትብለፅ ለጠ/ሚ/ር መለስ የፃፈችውና ምንም ምላሽ ያላገኘው ደብዳቤ እንዲህ ይላል:-*

*«ለአቶ መለስ ዜናዊ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስfር*
*<u>አዲስ አበባ</u>*

*ክቡር ጠ/ሚኒስfር፦ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ የእርስና የትግል ጓዶች፣ በአጠቃላይም ሰፊው የሃ ገራችን ሕዝቦች ሲመኙትና ሲታገሉለት የቆዩት አላማ እውን በመሆኑ ለሰላም፣ ለዕ ድገ፥ና ለዴሞክራሲ ፅኑ መሰረት መጣል በመቻሉና እርስም የተሻለ ለመስራት፣ ሕዝባችንን ለማገልገል የሚችሉበት የተሻለ ሁኔ ታ በመፈጠሩ በቅድሚያ እንኳን ደስ አለሎት ለማለት እፈልጋለሁ።*

*ክቡር አቶ መለስ!*

*ሌላ አማራጭ መንገድ ባለማግኘቴ ይህችን ማስ ታወሻ ለመላክ የተገደድኩ ሲሆን፣ እርስዎ ዘንድ ብትደርስልኝ ለደረሰብ ን ችግር መፍትሄ እንደምትለግሱኝ እምነቴ ፅኑ ነው።*

*እኔ ትብለፅ ዘርኡ ገሰሰ እባላለሁ። ዘርኡ ገሰሰ (አግአዚ) ግንባር ቀደም የሕወሓf የትግል አጋር አንዱ መሆኑን ለእርስዎ ከዚህ በላይ ማስታወስ አስፈላጊ አይመስለኝም። ስለ እኔ ሁኔታ ከዚህ በፊት የሚያውቁት ነገር ሊኖር የሚችል አይመስለኝም። ነገር ግን ከእርስ ዘንድ ቅርበት*



*ያላቸው ጥቂት ሰዎች በአካልም ጭምር የሚያውቁ ኝ ቢሆንም ስለደረሰብኝ ችግርና ስላለሁበት አስከፊ ሁኔታ ግምትና ክብ ደት ሰጥተው ግን አያውቁም። እኔ ለብዙ ዓመታት በአስመራና በሁመራ ያለምንም ረዳት ስንከራተት የቆየሁ በመሆኔ በትምሕርf በ፻ኩል ብዙ አልገፋሁም። በመሆኑም ችግሩ በጣም የበዛብ ኝና የተደራረበ ፣ ኑሮዬን ለማሸነፍ ያልቻልኩ ወይም የልታደልኩ ፍጠር ኘኝ። እናም ለአቀረብ፻ኩት ማስታወሻ ጊዜና ቦታ የሚ ሰጡት መሆኑን እያመንኩ ምላሹዎን በፅኑ ተስፋ እጠባ በቃለሁ።*

*ትብለፅ ዘርኡ*

*(አድራሻ አለው)....»*

*..የአግአዚ ልጅ ለዓመታት ብትመላለስም ሰሚ ባለማግኘቷ ተስፋ ቆርጣ እንደተወቸው ትገልፃለች። በዚሁ የመከራ ሕይወት ውስጥ እያለች በቅርቡ አንድ አስደንጋጭ ክሰተት በአዲስ አበባ መፈጠሩን ትሰማለች። ይህም በአግአዚ ስም የሚጠራው የመከላከያ ሰራዊት በመዲናችን የፈፀመው ዘግናኝ ተግባር ነበር። ትብለፅ እንዲሕ ትላ ለች፦ «የእኔን ማንነት የማያውቁ ሰዎች ከዚሁ ሰራዊት ጋር በተያየዘ አግአዚ ማለት ትርጉሙ ራሱ ምንድን ነው?...እያሉ ጠይቀውኛል። ያም ሆነ ይሕ አባቴ አግአዚም ሆነ እሱን የመሰሉ ታጋዮች የሞቱት ለታላቅ ክቡር አላማ ነው።*

*አአባቴ መጀመሪያ በረሃ የወጣው ለሰው ልጆች ወይም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት ሲል ነው:: እሱ ለሕዝብ መብትና ነፃነተ ሲል ነው የሞተ ው፤ የተሰዋው:: እኔ ልጁ በአባቴ የተሰየመው ጦር (አግአዚ ጦር) የፈፀመውን ድርጊተ ስሰማ በጣም ይቀፈኛል:: አባቴም ሆነ ሌሎች ታጋዮች ለሕዝብ ነፃነት እንጂ የሞተቱ:- ዜጐችን በጅምላ ለሚገ ድል አላማ አልተዋደቁም» በማለት አያይ ዛም:-*

*«ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት አብይ ነጥብ አለ:: ይህም በአግአዚ ስም የተሰየመ ውን ጦርና ለሰው ልጆች መብት እንዲሁም ለዴሞ ክራሲ ስርዓት ሲል የተሰዋውን ወይም ክቡር ሕይ ወቱን የሰጠውን አግአዚን ነጣጥሎና ለያይቶ መመልከት እንዳለበት ማስገንዘብ እሻለሁ:: አ! አግአዚ ለዚህ አይደለም የሞተው፤ አንድም ሰው ቢሆን መሞት የለበተም:: ያ እንዳይሆን ነው አግአዚና ታጋይ ጓዶቹ መራራውን ትግል በማካሄድ ት ልቅ መስዋዕትነትነ ፍለው ያለፉት» ብላለች::*

*በመጨረሻም ባስተላለፈችው መልዕክት:- «በሰላማዊ ዜጐች ላይ መፈፀምና መሆን የሌለበት ነገር ነው የደረሰው:: እኔ እንጃ እንዴት አድርጌ የተሰማኝን ጥልቅ ሃዘን እንደምገልፅ አላውቅም:: ለተከሰተው ጥፋ እንዲሕ ብዬ ለመናገር ቃላት ያጥረኛል:: የውስጤ ሃዘን ከምገልፀው በላይ ነው:: ደግሞም የአግአዚና የሌሎች ታጋዮች አላማ ከተሻረና መስዋዕ ትነታቸው እንደማንኛውም ሞት ከተቆጠረ ስለነሱ ማንሳት ተገቢ አይደደም:: እናም አግአዚ «ሞቷል» ከተባለና ሞቱ እንደተራ ነገር ከተወሰደ በእሱ ስም (በአግአዚ) መነገድ የለበትም:: ለሕዝብ ብሎ እስከሞተ ድረስ ምንም ይሁን ምን ሕዝብን የሚጐዳና የሚያሳዝን ነገር በስሙ ማድረግ አልነበረባቸውም፤ አይገባቸውም:: አግአዚ ለግሉ፣ ለቤተሰቡ፣ ለጥቂ ቶች ወይም ለእኔ ልጁ ጥቅም ለማስገኘት ብሎ አይ ደለም በወጣትነቱ ሞትን የመረጠው:: አላማው በግልፅ ይታወቃል:: ምንም እንኳ እኔ ልጁ ለችግር ተጋልጬ፣ በትግል ጓደኞቹ መጠለያ እንኳ ተነፍጌ የጐዳና ሕይወት ለመግፋት ብገደድም...የበለጠ የከፋኝ ግን የአግአዚ ስም በሌላው ዓለም ሳይቀር እየተነሳ፣ የእሱ የተከበረ አላማና የሞተበት ቁም ነገር ወደ ጐን መገፋቱ ነው:: በእሱ ስም የሚጠራው ሰራዊት በወሰደው አስደንጋጭና የሚያሳዝን እርምጃ «አግአዚ» የሚለው አብሮ እየተነሳ እንደጨካኝ አረመኔ ነው እየተፈረጀ ያለው:: ይህ በጣም ያሳዝናል:: ለዚህም ነው በአግአዚ ስም መነ ገድ የለበትም የምለው» ስትል ንግግራን በሲቃና ሃዘን ጭምር ነው የቋጨችው::*

*ምንጭ፡-* ኢትዮጵ